# ዓመታት ያካተተ እውነት እንዲሁም ለዘመናት ያልተቋረጠ ውሸት

ከዩሱፍ አደም

አቶ ጌታቸው ረዳ እንደ መንደርደሪያ አርገው መነሻቸው ያደረጉት ሕዝብ የማወቅ መብት አለው የሚለውን ትልቅ ቁምነገር ነው። ምሁራንም ከዴሞክራሲ ጋር እጅግ የተያያዘውን የማወቅ መብትን ለሕዝብ በማቅረቡ ይስማማሉ። ከዚህ አያይዘው የኢትዮ-ፓትርዮትን ድህረገፅ በጣም ሲያመሰግኑ፣ የአሲንባን ድህረገፅ፣ ዋለልኝንና ኢሕፓን በመተቸቴ ፅሁፎቼን አላወጣም ስላሉኝ፣ ተጣልቼ ተለይቻለሁ ብለዋል። አንዱን አመስግነው ሌላኛውን በጠብ ተለይተዋል።
በግሌ ሕዝብ የማወቅ መብቱን የሚያንገበግቡለት ከሆነ ሕዝብ አያውቅም የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ከየት አምጥተው ነው እርሶንና መሰሎችን አዋቂ አርገው የመደቡት? ህወኀት የፖለቲካ ሥልጣንን ከያዘበት ጀምሮ በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የፈፀመውን ግፍና በደል እኔና እርሶ ከሱ የበለጠ እናውቃለንን? እንደ ሕዝቡስ በወያኔ አገዛዝ ተርበናል፣ ተጠምተናል፣ በፌደራል፣ በአጋዚ፣ በልዩ ፖሊሳቸው ተጨፍጭፈናል? የዓለም ሕዝብ በማያውቀው ድብቅ እሥር ቤቶቻቸው ታምቀናል? የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ ጋር እያካሄደ ያለው አመፅ በቅድሚያ እራስን ቀጥሎም ጠላትን በሚገባ ማወቅን ጠያቂ ነው። ይህ ደግሞ በራሱ የጠራ የትግሉ ዓላማን መያዝ፣ ዘላቂ ጠላትን ማወቅና ከዘላቂ ወዳጅ ለይቶ ማስቀመጥን ግድ ያላል። እኔ ከፅሁፍዎ እንደምረዳው ዋና ጠላትዎ አርገው የወሳዱት እነዋለልኝንና ኢሕአፓን ነው። ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ የሆነቦት መሰለኝ። ተግባባን አልተግባባንም የኢትዮጵያም ሆነ የኢትዮጵያውያን ዋና ጠላት ወያኔ ነው። እዚህ ላይ የጠራ አቋም ይዘን እንረባረብ። ለመከፋፈሉና ሰርጐ ገብ በመሃላችን በመበተኑማ ወያኔ መች ሰነፈ።
ዋለልኝ የኢትዮጵያ የበኩር ልጅ ነው፣ ግንባር ቀደምም ጀግና። የኢትዮጵያ ሕዝብ በመሬት ከበርሬዎች መሬቱን ተነጥቆ የምድር ፍዳ እየተቀበለ ባለበት ጊዜ፣ በሙያ ማህበራት እንኳ መደራጀት የውሃ ሽታ ሆኖ በቀረበት ሰብዓዊም ሆነ ዴሞክራሲያዊ መብት የጥቂቶች ሆኖ በተወሰደበት፣ የሃይማኖት እኩልነት ባልተከበረበት፣ የብሄሮችና ብሄረሰቦች እኩልነት ቆጥ ላይ ተሰቅሎ ምድር ባልነካበት ጊዜ ዋለልኝ "ያበጠው ይፈንዳ፣ ኢትዮጵያ የብሄርና ብሄረሰቦች እስር ቤት መሆኗን ገልፆና ፅፎ" ሕይወቱን ሰጠ።
አቶ ጌታቸው ረዳ! እርሶ አሜሪካ ቁጭ ብለው ኃያሉን መንግሥት ጥላና ከለላ አድርገው በዋለልኝና በኢሕአፓ ላይ ሲወርዱ ምን ይሰማዎት ይሆን? ቢያንስ የሞራል ተጠያቂነት መኖሩን ስተውት ይሆን?።
የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለበትን የሥቃይ ሕይወት እራሱ ያውቃል። በመራራ ትግሉ ለዘላላምዊ ነፃነት ውድ ህይወቱን እየከፈለ ነው። ጆሮ ያለው ይስማ ዓይን ያለውም ይይ እያለም ነው። ለኛ በውጭ ላለነው ልጆቹም ጥሪውን እያስተላለፈ ነው። በደሌ የሚሰማችሁ፣ ሥቃዬ የሚሰቀጥጣችሁ ኑና ከጐኔ ቁሙ፣ የኔን ኑሮ እየኖራችሁ እኔን መስላችሁ አደራጁኝ እያለን ነው። ሰማን አልሰማነው ግን የየግል ውሳኔአችን ነው።
አቶ ጌታቸው ረዳ የአገራችን ገዳሞች ጥልቅ ዕውቀት የሚሰጡባቸው የዕውቀትና የስነ ፅሑፍ አድባራት ነበሩ። የዓለም አገሮች እንዴት እንደሚተዳደሩ ግራ ገብቶአቸው ሲተራመሱ የኢትዮጵያ ገዳማት ክብረ መንግሥትን በብራና ፅፈው ለዓለም ምሳሌ ሆነዋል። የነያሬድ የሙዚቃ ዕውቀትም ከነዚሁ ገዳምና አድባራት የመነጨ ነው።

ወያኔ ለኢትዮጵያ ሀገራዊ ለዓላዊነት፣ ለህዝቦቿ ዴሞክራሲያዊ እኩልነት በተለይም ለአማራው ብሔር ያለው ጥላቻ የትግሉ ዋነኛው መመሪያው ነው። ይህንን የፖለቲካ አቋሙን አሌ የሚል ካሉ የወያኔን 1967 ዓ·ም ማኒፌስቶ ይመልከቱ።
እርሶ ዋለልኝና ኢሕአፓን በመተቸቴ በድህረ ገፃቸው ፅሑፌን እንዲያወጡልኝ ብልክላቸው አላወጣ ስላሉኝ ተጣልቼ ተለይቻቸዋለሁ ብለዋል። አቶ ጌታቸው ትንሽ የቸኮሉና የተጣደፉ ይመስለኛል። አሲንባዎች ከስማቸው መረዳት

እንደሚቻለው ከወያኔና ከሻቢያም ጋር ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለአገሪቱ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብት ሲታገሉ የነበሩና፣ ገሚሶቹ ቆስለው፣ ገሚሶቹ በወያኔና በሻቢያ ደብዛቸው ጠፍቶ የነበሩ፣ ገሚሶቹም የተገደሉ ናቸው።

ዛሬ በአሲንባ የሚካፈሉ ግለሰቦች በስደት ህይወት ያለው ኑሮ ከባድ ቢሆንም የቆሙለትን ዓላማንም ሆነ የወደቁትን ጓዶቻቸውንም ክብር ሳይነፍጉ "ለትግሉ ነው ሕይወቴ" የሚለውን መፈክር አንግበው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሁለገብ መብት መሟላት የተቻላቸውን እያደረጉ ናቸው። ከኢሕአፖም ሆነ ከሌላም ተፅእኖ ነፃ የሆኑ ግለሰቦችም ናቸው። ይህንን አቋማቸውን እነሱን በማነጋገር ማረጋገጥ ይቻላል። ኢሕአፖም ሆነ አሲማባዎች የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች በየራሳቸው ለመመለስ ብቃት እንዳላቸው በግሌ አልጠራጠርም።

ወያኔና ሻቢያ ፀረ ኢትዮጵያ ናቸው። ያ ትውልድ ያነሳቸው ጥያቄዎች ዛሬም አለመመለሱ እስከ ዛሬ ለቀጠለው ችግር ዋነኛ ምክንያቱ ነው።

እነዚህ ጥያቄዎች፡-

1. መሬት ላራሹ፡-
2. ሁሉን ያካተተ ጊዜያዊ ሕዛባዊ መንግሥት፡-
3. የሠራተኛው፣ የአስተማሪው መብት መከበር፡-
4. የሴቶች ዕኩልነት ከአድሃሪ ባህልና የወንድ የበላይነት ተፅዕኖ ይላቀቅ፡-
5. የሃይማኖት እኩልነት ይከበር። መንግሥት በሃይማኖት፣ ሃይማኖት በመንግሥት አይግቡ፡-
6. የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶች ይከበሩ፡-
7. የማህበራዊና የኢኮኖሚ ዕድገት ለሁሉም፡-
8. የዘርና የክልል ፖለቲካ ይወገድ፣ የሁሉም ቋንቋና ባህል ይከበር፡-
9. አገር ተረካቢውን ወጣት ትውልድ የሚበክሉ ልምዶች ሁሉ ይወገዱ፡-
10. የፓርቲዎችንም ሆነ የገዢዎች ጥቅም ሳይሆን፣ የሀገርን ድንበር የሚጠብቅ ሀገራዊ ጦር ይመሥረት። የወያኔ ዘረኛና የአካባቢ ወይም የወያኔ ተለጣፊዎች ጦር ይፍረስ፡-
11. የኢትዮጵያ ለዓላዊነት ይከበር፡-

ከላይ የተዘረዘሩት መሠረታዊ ሁኔታዎች ዕውን እንዲሆኑ ግን፣ የወያኔ ዘረኛ ቡድን ከሥልጣን መወገድ አለበት። ዜጐች በየትኛውም የአገራቸው ክፍል መንቀሳቀስ መኖርና መሥራት መቻል ይኖርባቸዋል። ዛሬ እንደሚታየው የክልል አንድ ተወላጅ ብቻ ነው በድፍን ኢትዮጵያ መንቀሳቀስ መሥራትና መኖር የሚችለው። ከትግራይ ክልል የሚመጣው፣ ለሚሰራው ጥፍትና በህዝብ ለሚያደርሰው በደል "ሕጋዊ" ሽፋን የሚሰጠው ለዚሁ ክልል ዓባላት ብቻ ነው።

ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ እሱ ካለፈም በኋላም የሚቆዩ በርካታ ችግሮች አቆይቶናል። እነዛንም ችግሮች ካሁኑ መረዳት፣ ለመፍትሄአቸውም መዘጋጀት ያስፈልጋል። የኢትዮጵያን የአገር ክፍል ቆርጦ ለሱዳን አስረክቧል፣ መሬቷን ለቻይና፣ ለቱርክ፣ ለህንዶች ለአረቦች ቸርችሮ ገንዘቡን በኪሱ አስገብቷል። የኢትዮጵያን የታሪክ ቅርሶች፣ የቤተክርስቲያን አልባሳትን ሳይቀር ለባዕድ አገሮች በጨረታ ሸጧቸዋል።

ከስልጣን ሲወገድም በአገራችን ብዙ ችግር የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን አዘጋጅቷል። ለም የሆነውን የጐንደር ክፍል ወደ ትግራይ ክልሎ ነዋሪውን የአማራ ብሄር በማባረር ጡረታ ወጡ የሚላቸውን ወታደሮች ከነሙሉ ትጥቃቸው በአራሽነት አስፍሯል። ዋና ከተማው በመብራት እጦትና በውሃ ጥማት እየተሰቃየ፣ ግቤ አንድና ሁለት ተገድበው በአካባቢው ነዋሪ የሆነው ህዝብ ያለችውን ቅንጣት የእርሻ ቦታ የሚያጠጣው ውሃ እያጠረበት፣ አሣ አጥማጅ የሆነውም አሣዎቹ እየሞቱበት፣ መብራት ለኬንያ ለኡጋንዳ እየተሸጠ የስቃይ ኑሮውን እንዲቀጥል የተገደደበት ሁኔታ ውስጥ ተዘፍቆ እየኖረ ነው።

ዋናውና ትልቁ ቁምነገር ሁላችንም ማውቅና መገንዘብ ያለብን የትግራይ ህዝብና ወያኔ አንድ አለመሆናቸውን ነው። የትግራይ ሕዝብ ዛሬ በማያውቀው የፍራቻ ባህር ተዘፍቆ እየኖረ ነው። እኔ ከሥልጣን ከወረድኩ አማራው ይፈጅሃል፣ ያስገኘልንህን ነፃነት ሁሉ ይነፍግሃል፣ ይዞታህ ይጠባል ... ወዘተ እየተባለ በጨለማ ቤት የሚኖር ሕዝብ ነው።

የሚያሳዝነው ነገር ግን፣ ተማርን አውቅን የሚሉት ከትግራይ ሕዝብ የተፈጠሩ ግለሰቦች በዚህ መከራ ጊዜ ከጐኑ አለመቆማቸው ነው። ማጋነን ካልሆነ ከ 95% የማያንሱት በቀጥታ ወይም በስውር ከወያኔ ጋር ቆመዋል። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የወያኔን አጀንዳ አስፈፃሚ ሆነዋል። በወታደርነት፣ በፖሊስነት፣ በስላይነት፣ በሰርጐ ገብነት፣ በምሁርነት እያገለገሉት ያሉት እነሱ ናቸው። ዝናብ ይዘንባል፣ ግን የተፈጥሮ ህግ በመሆኑም ያባራል። ሲያባራ የትግራይ ህዝብ ምን ሊደርስበት ይችል ይሆን የሚለው ግን እነሱን አላሳሰበም።

ይህ ግፍና በደል ለዓመታት የተፈፀመበት ሕዝብ በግብታዊ እርምጃም ቢሆን በትግራይ ሕዝብ ላይ ሊነሳ ይችላል። ከትግራይ የመጡ ምሁራን ለምን ይህንን ሁኔታ ማየት ተሳናቸው?

ይህ ጥያቄ ከትግራይ ለመጡ ምሁራን ብቻ የሚቀርብ ጥያቄ አይደለም። በእኩልነት ደረጃ ለኤርትራ ምሁራንም መቅረብ የሚገባው ጥያቅ ነው። የኤርትራ ሕዝብ ለብዙ አመታት ታግሏል። መጨረሻው ግን የነፃነት መደምደሚያው ባርነት ሆኖ ቀርቷል። አምባ ገኑን መቃውም ባቻ ሳይሆን፣ የተለየ ሃሳብና መፍትሄን የሚያመለክቱ ፅሑፎችን ማናበብ ጭምር ሕይወትን የሚያስከፍል ሆኗል። የኤርትራ ወጣት ለከፋ ሥደት፣ ለአረብ አገር ባርነት፣ ለባሕር አሳነባሪ ቀለብ እየሆነ ነው። እኔ በምኖርበት የምዕራብ ኤውሮፓ አገር ሥራ የሌላቸው ኤርትራውያን ሳይቀሩ በሥራ አጥነት ከሚያገኙት ገንዘብ 2 ከመቶ እንዲከፍሉ ይገደዳሉ። ካልከፈሉ ወላጆቻቸውና ዘመዶቻቸው ለከፋ እሥር ይዳረጋሉ።

ዛሬ የትግራይ ሕዝብም ሆነ የኤርትራ ሕዝብ ታሪክ በወያኔ የአገዛዝ ዘመን የተገላቢጦሽ ሆኗል። የሞሶሎኒ ፋሽሽት ኢትዮጵያን በቅኝ አገዛዝ ሥር ለመጣል ዘመቻ በተከፈተበት ጊዜ በዋና ከተማችን በአ/አ በግራዚያን ላይ ቦንብ ጥለው ያቆሰሉት አብረሃም ደቦጭና አስግዶም ነበሩ። አቡነ ጴጥሮስ ለሊቱን በሞላ በአፄ ሚኒሊክ ቤተመንግሥት ስየል ሲፈፀምባቸው አድረው፣ የጣሊያንን የበለይነት አልቀበልም በማለታቸው፣ በማግሥቱ ዛሬ በአ/አ የአቡነ ጴጥሮስ አደባባይ በሚባለው ቦታ መላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዚህ ፋሽሽት እዳይገዛ ገዝተው ሲረሸኑ ፣ የረሸኗቸው ከኤርትራ የተወለዱ አስካርያን ነበሩ። በተቃራኒው ደግሞ ጣሊያን በምርኮኛነት ከወሰዳቸውና የጣሊያን አሽናፊነት በአደባባይ እንዲያሳይ የኢትዮጵያን ባናዲራ መሬት ላይ አንጥፈው፣ ለሕዝብ በሽለላ ትርዕይት እንዲያሳይ የተጋበዘው ከኤርትራ ህብረተሰብ የተወለደው ዘርዓይ ይድረሰ የተነጠፈለትን ባንዲራ ብድግ አርጐ በመሳም በተቃራኒው ሳንጃውን ከአፎቱ በማውጣት በጣሊያኖች ላይ አሳረፈ። የኢትዮጵያ ሕዝብ የበኩር ልጅ መሆኑንም በመስዋዕትነቱ አረጋገጠ።

በኢትዮጵያ ላይ የነገሱትም ነገሥታት ጥሩም መጥፎችም ነበሩ። የነገስታቱም ሆነ የአጠቃላይ ሕዝባችን እድገት ከጊዜ ጋር የተዛመደ ነው። ከነበሩበት የታሪክ ጊዜ ውጭ መገምገም የለባቸውም ። የምንጠብቅባቸው ነገርም አይኖርም። ይህ ማለት ግን ኃ/ሥላሴና አፄ ሚኒሊክ አንድ ናቸው ማለት አይቻልም። አፄ ኃ/ሥላሴ “ሞ አንበሳ ዘዕመነገደ ይሁዳ ሥዩመ እግዚአብሄር ዘኢትዮጵያ“ እንዳሉት ሳይሆን ፣ አፄ ኃ/ሥላሴ ለስልጣን ያበቃቸው መለኮታዊ ሃይል ሳይሆን ምድራዊ የሆነ ነጭና ባዕድ ኃይል መሆኑ የማይካድ ሀቅ ነው።

መንግሥት ለቆመለት የኅብረተሰብ ክፍል በጥቅም አስጠባቂነት ይሠራል። የራሳችንን ተመክሮ ስንመለከት የአፄው መንግሥት በአማዛኙ የንጉሳዊ ቤተሰብና የመኳንንቱ፣ የባለመሬቶችና ከባዕድ ጋር በጥቅም የተቆራኙ ከበርቴዎች ጥቅም አስጠባቂ የነበረ ሲሆን። ብዙውን ጨቁኗል፣ በድሏል፣ አሰቃይቶና አንበርክኮ ገዝቷል።

ያ መንግሥት የጥቂቶች ጥቅም አስጠባቂ ሆኖ የብዙሐኑን ጥቅም የተጻረረ በጠላትነት የተሰየመ መንግሥት ነበር። በአብዮት መወገድ የነበረበትም ለዚህ እንደነበር አይሳትም። መንግሥት የማነው ለሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ ለመስጠት የሀገሪቷን አንጡራ ሀብት በተመለከተ፣ የምርት ውጤቶቿን በተመለከተ፣ የልማት ፈሰሶችን፣ ኢንዱስትሪዋን … ወዘተ የሚያስጠብቀውንም የባዕድ ኃይል ጥቅም እንዲሁ መጤን ያሻል። መንግሥት ራሱን በቅጽሎች አሸብርቆ ሕዝባዊ ነኝ ቢልም ”ድመት ብትመነኩስ ዓመሏን አትረሳ” ነውና የመንግሥትን መሠረታዊ ወገንተኛ ሚናን በተግባሩ የማንን ጥቅም እያስጠበቀ እንደሆነ በተጨባጭ በመመርመር ምንነቱን በተሻለ ማወቅ ይቻላል። በሀገራችን ታሪክ የሴት ልጅ እኩልነት ያልተከበረበትና በወንዶች የባላይነት ሥር የወደቀበት ሁኔታ ለዘመናት ቆይቶል። ዛሬም ሙሉ ለሙሉ የተወገደ አይደለም ። የህፃናት አስተታደግ ባህልም እንደዚሁ የሚያሳዝን ነው። እንግዳ ቤት ሲመጣ ከቤት ውጡ እየተባልን የመስማትና የማድግ፣

የመጠየቅና የማወቅ መብት ሁሉ ተነፍገን ማደጋችን ግልፅ ነው። ዝም በይ፤ ዝም በል እየተባልን በአለንጋ እየተጠበጠብን ማደጋችንም መጥፎ ባህል ነው። ቄስ ት\ቤት ስንማር በአለንጋ ሲጠፈጥፉን ለዋሉት ቄስ ያቺ የመከራ ቀን ስታልቅ "የየኔታን ጠላት በብረት ቁልፍ" በሉ እንባላላለን።

አቶ ጌታቸው አገራችን በጣም ብዙ ጠላቶች በውስጥም በውጭም እያላት ከኢሕአፓ ጋራ ላለመግባባት ምክንያቶ ምን ይሆን? በኔ እምነት ዛሬ ሁላችንም ኃይላችንን አስተባብረን መነሳት ያለብን፣ ሕዝባችንን ለመከፋፈል አገራችንን ለመበታተን የተነሳው ጐጠኛውና ዘረኛው የወያኔ ቡድን እያለ ለምን ከኢሕአፓ ጋር አምባ-ጓሮ መጫር አስፈለገ?

ኢሕአፓ ከተመሠረተ ጀምሮ ከውስጥም ከውጭም በርካታ ጠላቶች ተነስተውበት ነበር። አፄ ኃ/ሥላሴ ገና በእንጭጭነቱ፣ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም፣ ወያኔ፣ ሻቢያ፣ … ወዘተ· በድርጅቱ የአመራር አባላት ላይ ዘምተዋል። ይህ ሁሉ ሆኖ ገሚሶቹ ሲጠፉ ገሚሶቹም ኢሕአፓን ማጥፋት ግን አልተቻላቸውም።

ለምን አልተቻላቸውም የሚል ጥያቄ ማንሳት በተገባቸው ነበር። ለዚህ መሆን ዋነኞቹ ምክንያቶች፡-

ሀ) ይዟቸው የተነሳው ጥያቄዎች ሕዝባዊና አገራዊ በመሆናቸው፣

ለ) ዓመታት ቢያልፉም እነዚህ ጥያቄዎች እያደር በህዝቡ ልቦና እየሰረፁ በመግባታቸው፣

ሐ) ለዓላማው፣ ለሕዝብ ፍቅርና ለሀገሪቱ ለዓላዊነት ውድ ሕይወት መክፈልን እንደ ፀጋ በመቀበሉ ነው፣

መ) በኢሕአፓ ሥር ተካተው የታገሉት ተገደው ሳይሆን በሙሉ ፈቃደኝነት ለሕዝባቸው ከፍተኛ ፍቅርና ክብርም ሰላላቸው ነው፣

ሠ) ከመከራውና ሥቃዩ የተረፉ የዛ ስምዓታት እናትና አባቶች፣ እህትና ወንድሞች ዛሬም በልባቸው የሃዘን ከል እንደለበሱ ናቸው፣

አቶ ጌታቸው! የኢሕአፓ አወቃቀርም ሆነ አሰራር ለዚህ የሚያመች አይደለም። ከአመራር አካል አባላቱም በውጭ አገር የሚኖሩት በቁጥር በጣም አነስ ያሉት ናቸው። በርካታ ቁጥር ያላቸው በሀገር ቤት በሕቡዕ የሚኖሩና በህቡዕ የሚንቀሳቀሱ አመራርም የሚሰጡ ናቸው። በየፋብሪካው በሠራተኝነት ተቀጥረው፣ በገጠሩም የገበሬውን ኑሮ እየኖሩ፣ በት/ቤቶችም ውስጥ በመምህርነት እየተቀጠሩ በህቡዕ የሚደራጁና የሚያደራጁም ናቸው።

ወያኔም ይህን ስለሚያውቅ አንድ ጊዜም የኢሕአፓ አባል ወይም አባሎች ይዣለሁ፣ ለፍርድ ቀርበው ይሄን ያህል ዓመት ተፈርዶባቸዋል ሲል አልተሰማም። የድርጅታቸውን ሚስጥር ትንፍስ ሳይሉ፣ ከህንፃ ላይ የተከሰከሱ፣ የነ ተስፋዬ ደበሳይን ጥይታቸውን ጠጥተው የሞቱ፣ የነጋይም ታሪክ በሚገባ ያውቃል። ይሄን ያህል የዚህ ወይም የዛኛው ድርጅት አባላት ተይዘዋል ለፍርድ ቀርበዋል፣ ይህን ያህል በምህረት ተለቀዋል እያለ ሲቀላምድ ኢሕአፓ የሚል ሥም ሲጠራ አልተሰማም።

እርሶ ደግሞ ከአመራር አካል አባላት ኢያሱ አለማየሁን ብቻ መርጠው የብዕር ጦርነት ከፍተውበታል። ፅሁፎን ሳነብ አንደኛውን መፅሐፍ እየጠቀሱ "እንደሰማሁት የታተመው አ/አ ነው" …ወዘተ· እያሉ ያብጠለጥሉታል። አ/አ ታተመ ቢባልስ ወያኔ ነው ያሳተመለት የሚያሰኝ ይሆን? ። ኢሕአፓ እኮ በፋሽሽት መንግሥቱ ጊዜም አ/አ መፃህፍት አሳተሟል፣ እንደጐህ ያሉትን ዝነኛና አስተማሪ የሆኑ መፅሄቶችን እያሳተመ ለገበያ በማዋል የሕዝባችንን ንቃት አሳድጓል። ደርግ አዲስ ገንዘብ ባሳተመበት ጊዜ እንኳን ኢሕአፓ በህብዕ በመግባት በብሩ ላይ በረቀቀ መንገድ ማንነቱን አሳይቶል።

እርሶ መፅሐፍ አሳትመው አይደለም ወይ? ልዩነት አለው ካሉኝ፣ እርሶ በስማ በለው ሰማሁ እንዳሉት ልዩነቱ፣ እርሶ በአሜሪካ ኢያሱ በአ/አ ማሳተማችሁ ብቻ ነው። ኢትዮጵያ ዴሞክራሲ የለም፣ አሜሪካ ግን አለ፣ የሚሉኝ ከሆነ የትኛው ዲሞክራሲ እንደአለ፣ እባኮ ያስረዱኝ። አሜሪካ ከነማርቲን ሉተር ኪንግ (Martin Luther King) ጊዜ ጀምሮ ስንት ጥቁር ሕዝብ በጥይት እንደረገፈ፣ እስከዛሬ ድረስም ስንቱ በፖሊስ ጥይት እየተገደለና ካለፍርድ በየእስር ቤቱ ታጉሮ እንደሚኖር እርሶ ሳያውቁት ቀርተው ነው? እነ ጆርጅ ዋሽንግተንና መሰሎቹ የየራሳቸው ባሮች እንደነበራቸው አያውቁምን??

ወያኔንስ ደግፎና አቅፎ ለሥልጣን ያደረሰው ማነው?። ጥይትና ወታደራዊ ሥልጠና እየሰጠው ሕዝባችንን የሚያስፈጀው አሜሪካ መሆኑን ስተውት ይሆን? በአፍሪቃ፣ በላቲን አሜሪካ፣ በእስያ አምባገነን መሪዎችን ለሥልጣን አብቅቶ የሚያሰቃየውስ ይኸው መንግሥት መሆኑን አያውቁም?።

በአፍጋኒስታን፣ በሊቢያ፣ በየመን፣ በፓኪስታን የሚወርደው ቦንብስ የማነው?። በአሜሪካ በሚጣለው ቦንብ የረገፉት ህፃናት፣ አዛውንትና ሴቶች፣ የተበከለው የአየር ንብረት መጠኑን ማን ያውቃል?። ከሁሉም በላይ ግን ይህንን ዓለም አቀፍ አንባ ገነን መንግሥት የትኛው ፍርድ ቤት ይከሰስና ፍትዕና ርትዕ ይከበራሉ?

አቶ ጌታቸው እስቲ ዕይንታዎን ሰፋ ያርጉና ይህ የሚኖሩበት አገር መንግሥት ለወያኔ የሚያደርገውን ሁለገብ እርዳት እንዲያቆም ይፃፉ!! ይህንን መሰል ተግብር ከሚቃወሙ ኢትዮጵያን ጋር በመተባበር በመምከር ችግራችን በዓለም ደረጃ ታዋቂነት እንዲያገኝና የፖለቲካ ድጋፍ እንዲያገኝ ሠልፍ ይውጡ፣ ወያኔን ለማጋለጥ ይተባበሩ። በዚህ ፅሁፍ ስለ ኢሕአፓ የማውቀውን ያህል ላስረዳዎት ጥረት አድርጌአለሁ። ጠላቶ ያልሆነን ጠላት በመፍጠር እራሶን አያዳክሙ። በተረፈ ኢሕአፓ እራሱን ከጥቃት መከላከል መቻሉን አይጠራጠሩ። ለዚች ፅሑፍ የተሟላ መልስ እንደሚልኩልኝ በመተማመን እኔም በትዕግሥት እጠብቃለሁ።

ከዩሱፍ አደም